በቤ/ጉ/ክ/መንግስት በግል ወይም በማህበር የኦዲት እና የሂሳብ አያያዝ ለሚሰሩ ባለሙያዎች የሙያ ፍቃድ አሰጣጥ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር-109/2009

መግቢያ፣

በክልላችን ዉስጥ የሚሰጠውን የኦዲት እና የሂሳብ ስራ አገልግሎት ሙያው የሚጠይቀዉን ችሎታ፤እዉቀት እና ስነ-ምግባር ባላቸው ባለሙያዎች እንዲሰጥ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

የኦዲት እና የሂሳብ አያያዝ ባለሙያዎችን የሙያ ብቃት በየጊዜው በማረጋገጥ የአገልግሎቱን ጥራት ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመንግስታዊም ሆነ በግል ሴክተሮች የኦዲት እና የሂሳብ አያያዝ አገልግሎት ፍላጎት ሀገራችን እያስመዘገበችው ካለዉ ኢኮኖሚ አንጻር እየተጣጣመ በመሆኑ እንዲሁም የኦዲት እና የሂሳብ አያያዝ ሽፋንን ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኦዲት እና በሂሳብ አያያዝ አገልግሎት ስራ ላይ በግል ወይም በማህበር ተደራጅተው ለመስራት የሚፈልጉትን ባለሙያዎች ብቃታቸዉን በማረጋገጥ የሙያ ፍቃድ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልላችን ዉስጥ በመንግስት ድርጅቶች ፤በማህበራት እና በግል ተቋማት ትክክለኛ የሆነ የሂሳብ አያያዝ እንዲኖር ለማድረግ ክትትል እና ቁጥጥር አስፈላጊ በመሆኑ፤

የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በግል ለሚሰሩ ኦዲተሮች እና ሂሳብ አዋቂ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የመስጠት እና የማደስ እንዲሁም የግል ኦዲተሮች እና የሂሳብ አዋቂዎች የሙያ ደረጃዉን ጠብቀዉ ስራዎችን በአግባቡ ማከናወናቸዉን ለመከታተልና ለመቆጣጠር፤የማያከናውኑም ከሆነ የማገድ እና የመሰረዝ ስልጣን በህግ የተሰጠው በመሆኑ፤

የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትን ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን እንደገና ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ 119/2006 **አንቀጽ 28 ንኡስ አንቀጽ** (1) መሰረት የቤ/ጉ/ክ/መ/ምክር ቤት ከዚህ የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ በቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በግል ወይም በማህበር የኦዲት ወይም የሂሳብ አያያዝ ለሚሰሩ ኦዲተሮች እና የሂሳብ አዋቂዎች የሙያ ፍቃድ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 109/2009 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፡-

1/ ‹‹ ክልል ›› ማለት የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ነዉ፡፡

2/ ‹‹ **አዋጅ** ›› ማለት የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን እንደገና ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ 119/2006 ነዉ፡፡

3/ ‹‹ **አጭር ምዝገባ** ›› ማለት ከፌዴራል ወይም ከሌላ አቻ ክልል ዋና ኦዲተሮች መ/ቤት የኦዲት ወይም የሂሳብ ስራ የምስክር ወረቀት ያለዉ ሆኖ በቤ/ጉ/ክ/መንግስት ሊሰራ የሚችልበትን ፍቃድ እንዲያገኝ የሚደረግ ምዝገባ ነዉ፡፡

4/ ‹‹ **መስሪያ ቤት** ›› ማለት የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ነዉ፡፡

5/ ‹‹ **ሰዉ** ›› ማለት በግል ወይም በማህበር በመደራጀት የሙያ ፍቃድ የተቀበሉ ኦዲተሮች ወይም የሂሳብ ባለሙያዎች ማለት ነዉ፡፡

6/ ‹‹ **የሙያ ፍቃድ** ›› ማለት ብቃታቸዉ ለተረጋገጠላቸዉ ኦዲተሮች ወይም የሂሳብ ባለሙያዎች የሚሰጥ የሙያ ማረጋገጫ ፍቃድ ነው፤

7/ ‹‹ **የሙያ ማህበር** ›› ማለት በቤ/ጉ/ክ/መንግስት፤በሀገር አቀፍ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ እዉቅና ያለዉ እና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ወይም በቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት ተቀባይነት ያገኘ የኦዲት ሙያ ወይም የሂሳብ አያያዝ ማህበር ማለት ነዉ፡፡

8/ ‹‹ **ባለሙያ** ›› ማለት በዚህ ደንብ መሰረት የተመሰከረለት ኦዲተር ወይም የተመሰከረለት የሒሳብ ባለሙያ ፤በመ/ቤቱ የተመዘገበ እና የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነዉ፤

9/ ‹‹ **የሂሳብ ባለሙያ** ›› ፡- ማለት በሂሳብ ሙያ የብቃት ማረጋገጫ ኖሮት በግል ወይም በማህበር በሂሳብ አያያዝ ስራ ላይ የተሰማራ ማለት ነዉ ፡፡

10/ ‹‹ **የኦዲት ስራ ባለሙያዎች ማህበር** ›› ማለት በዚህ ደንብ ዉስጥ የተደነገገዉን መስፈርቶችን አሟልተዉ በቤ/ጉ/ክ/መንግስት የማህበራት አደረጃጀት ሕግ መሰረት ተደራጅተዉ ከአደራጅ አካል ህጋዊ ሰዉነት አግኝተዉ በቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዉስጥ የኦዲት ስራ አገልግሎት የሚሰጡ ነው፤

11/ ‹‹ **የሂሳብ አያያዝ ባለሙያዎች ማህበር** ›› ማለት በዚህ ደንብ ዉስጥ የተደነገገዉን መስፈርቶችን አሟልተዉ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት የማህበራት አደረጃጀት ሕግ መሰረት ተደራጅተዉ ከአደራጅ አካል ህጋዊ ሰዉነት አግኝተዉ በክልሉ ዉስጥ የሂሳብ ስራ አገልግሎት የሚሰጡ ማለት ነዉ፡፡

12/ ‹‹ **የምስክር ወረቀት** ›› ማለት ለኦዲት ባለሙያዎች ወይም ለሒሳብ አዋቂዎች ሙያዊ ብቃታቸዉን በማረጋገጥ በመስሪያ ቤቱ የሚሰጥ ማስረጃ ነዉ፤

13/ ‹‹ **ዳይሬክቶሬት** ›› ማለት በቤ/ጉ/ክ/መ/ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የኦዲትና የሒሳብ ሙያ ፍቃድ አሰጣጥ የኦዲት ጥራት የሚያረጋገጥ ዳይሬክቶሬት ነዉ፤

14/ ‹‹ **የኦዲት ቡድን** ›› ማለት የኦዲት አገልግሎት እንዲሰጥ የተፈቀደለት አካል ሆኖ አንድ የኦዲት ስራ ለማካሄድ ሲሰማራ ሁለት እና ከዚያ በላይ የኦዲት ባለሙያዎችን የያዘ ቡድን ነዉ፤

15. “ **የተፈቀደለት ሒሳብ ባለሙያ** (Authorized Accountant) ” ማለት የተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ በዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ የተመዘገበና የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

16/’ **“የተፈቀደለት ኦዲተር** (Authorized Auditor)” ማለት የተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ በዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደተፈቀደለት ኦዲተር የተመዘገበና የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

17/ ‹‹ **ፐብሊክ ኦዲተር** ›› ማለት የህዝብ ጥቅም ያለባቸዉን አካላት ኦዲተር ሆኖ እንዲሰራ በዋና ኦዲተር መ/ቤት ፈቃድ የተሰጠዉ የተመሰከረለት ኦዲተር ነዉ፤

18/ ‹‹ **የህዝብ ጥቅም ያለበት አካል** ›› ማለት የስራዉን አይነት ወይም ባህሪ፤የሀብቱን መጠን ወይም የሰራተኛዉን ቁጥር ከግምት ዉስጥ በማስገባት መስሪያ ቤቱ በየጊዜዉ ከህዝብ ጥቅም ጋር ከፍተኛ ትስስር አለዉ ብሎ የሚወስነዉ ሪፖርት አቅራቢ አካል ሲሆን በተለይም የሚወጣዉን የግዴታ ምስክር ወረቀት ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ግብይት ማዋል የሚችል ማንኛዉም ኩባንያን፤ ባንኮችን ፤የኢንሹራንስ ኩባንዎችን እና ማንኛዉንም ሌሎች የፋይናንስ ተቋማትን እንዲሁም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይጨምራል፤

19/ ‹‹ **ተቋማት** ›› ማለት ህጋዊ ሰዉነት አግኝተዉ በንግድ፤በአገልግሎት እና በልማት ስራ ላይ በመሰማራት አገልግሎት የሚሰጡ ማለት ነዉ፡፡

20/ “ **የሃላፊነት ደረጃ** “ ማለት በንግድ የሂሳብ አያያዝ ስራ አጠናክሮ የሚዘጋና የሂሳብ መዛግብት በማዘጋጀት የሚያስመረምር በስሩም ላሉ ሰራተኞች አመራር የሚሰጥ ሆኖ በስራ አጠራር የፋይናንስ ሀላፊ እንዲሁም በዉጭ ኦዲት ድርጅት ከፍተኛ ኦዲተር እና ከዚህ በላይ የስራ መደብ ላይ የስራ አመልካች ማለት ነዉ፡፡

21/ ‹‹ **ደረጃ 1(አንድ)የተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ** ›› ማለት በሁሉም ደረጃ ላሉት ተቋማት ወይም መስሪያ ቤቶች የሂሳብ ስራ አገልግሎት ለመስጠት በዚህ ደንብ መሰረት በመስሪያ ቤቱ የተፈቀደለት የሂሳብ አያያዝ ባለሙያ ማለት ነዉ፡፡

22/ ‹‹ **ደረጃ 2(ሁለት) የተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ** ›› ማለት የሂሳብ ባለሙያዎች በማህበር ተደራጅተዉ ወይም በግል አመታዊ በጀታቸዉ ወይም ገቢያቸዉ ብር 500,000,000.00 (አምስት መቶ ሚሊዮን ብር) እና ከዚያ በታች በሆነ ተቋማት፣ዩኒዬኖች፣መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ አገልግሎት እንዲሰጥ በዚህ ደንብ መሰረት በመስሪያ ቤቱ የተፈቀደለት የሂሳብ አያያዝ ባለሙያ ወይም በመስሪያ ቤቱ አጭር ምዝገባ ያደረገ ማለት ነዉ፡፡

23/ ‹‹ **ደረጃ 3(ሶስት)የተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ** ›› ማለት አመታዊ በጀታቸዉ ወይም ገቢያቸዉ ብር 100,000,000.00 (አንድ መቶ ሚሊዮን ብር) እና ከዚያ በታች የሆኑ ተቋማት፣ ማህበራት፣ ዩኒዬኖች፣መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ አገልግሎት እንዲሰጥ በዚህ ደንብ መሰረት በመስሪያ ቤቱ የተፈቀደለት የሂሳብ አያያዝ ባለሙያ ወይም በመስሪያ ቤቱ አጭር ምዝገባ ያደረገ ማለት ነዉ፡፡

24/ ‹‹ **ደረጃ 4(አራት)የተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ** ›› ማለት አመታዊ በጀታቸዉ ወይም ገቢያቸዉ ብር 10,000,000.00 (አስር ሚሊዮን ብር) እና ከዚያ በታች የሆኑ ተቋማት ፣ማህበራት፣ ዩኒዬኖች፣መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ አገልግሎት እንዲሰጥ በዚህ ደንብ መሰረት በመስሪያ ቤቱ የተፈቀደለት የሂሳብ አያያዝ ባለሙያ ወይም በመስሪያ ቤቱ አጭር ምዝገባ ያደረገ ማለት ነዉ፡፡

25/ “ **ኦዲተር** “ ማለት የኦዲት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ ኖሮት በኦዲት ስራ ላይ በግል ወይም በማህበር በመስራት የሂሳብ አያያዝ ትክክለኛነት፣ ምሉእነት እና የሂሳብ ሪፖርት በማረጋገጥ አስተያየት የሚሰጥ ማለት ነው፡፡

26/ “ **ደረጃ 1 የተፈቀደለት ኦዲተር** “ ማለት የኦዲት ስራ አገልግሎት በሁሉም ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተቋማት የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት በዚህ ደንብ መሠረት በመ/ቤቱ የተፈቀደለት ባለሙያ ወይም በመስሪያ ቤቱ አጭር ምዝገባ ያደረገ የተፈቀደለት ኦዲተር ማለት ነዉ፡፡

27/ "**ደረጃ 2 የተፈቀደለት ኦዲተር**" ማለት አመታዊ በጀታቸው ወይም ገቢያቸው ብር 500,000,000.00 / አምስት መቶ ሚሊዮን ብር / እና ከዚያ በታች በሆነ ማህበራት፣ ተቋማት፣ መስሪያ ቤቶች ዩኒዬኖች መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ኢንተርኘራይዞች የኦዲት ስራ አገልግሎት እንዲሰጥ በዚህ ደንብ መሠረት በመ/ቤቱ የተፈቀደለት ባለሙያ ወይም በመስሪያ ቤቱ አጭር ምዝገባ ያደረገ የተፈቀደለት ኦዲተር ማለት ነዉ።

28/ " **ደረጃ 3 የተፈቀደለት ኦዲተር** ›› ማለት አመታዊ በጀታቸው ወይም ገቢያቸው ብር 100,000,000.00 /አንድ መቶ ሚሊዮን ብር/ እና ከዚያ በታች የሆኑ ማህበራት ተቋማት መ/ቤቶች ዩኒዬኖች፣ መሰረታዊ የህብረት ስለራ ማህበራት ወይም ኢንተርኘራይዞች ላይ የኦዲት ስራ አገልግሎት እንዲሰጥ በዚህ ደንብ መሠረት በመ/ቤቱ የተፈቀደለት ባለሙያ ወይም በመስሪያ ቤቱ አጭር ምዝገባ ያደረገ የተፈቀደለት የኦዲት ባለሙያ(ኦዲተር) ማለት ነዉ።

29/ "**ደረጃ 4 የተፈቀደለት ኦዲተር**" ማለት አመታዊ በጀታቸው ወይም ገቢያቸው ብር 10,000,000.00 / አስር ሚለዮን ብር/ እና ከዚያ በታች የሆኑ ማህበራት፣ ተቋማት መ/ቤቶች፣ ዩኒዬኖች፣ መሰረታዊ የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ኢንተርኘራይዞች የኦዲት ስራ አገልግሎት እንዲሰጥ በዚህ ደንብ መሠረት በመ/ቤቱ የተፈቀደለት ባለሙያ ወይም በመስሪያ ቤቱ አጭር ምዝገባ ያደረገ የተፈቀደለት የኦዲት ባለሙያ ማለት ነዉ።

30/ "**ማህበር** " ማለት መሠረታዊ የህብረት ስራ ማህበር፣የህብረት ስራ ዩኒዬኖች፣የህብረት ስራ ፌዴሬሽን፣የልማት ማህበር፣የፋይናንስ ማህበር፣የልዩ ልዩ ሙያ ማህበር እና ማንኛዉም ህብረተሰባዊ ማህበር ማለት ነዉ።

አንቀጽ 3

የጾታ አገላለፅ

በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተገለፀዉ የሴትንም ጾታ ያጠቃልላል።

አንቀጽ 4.

የተፈፃሚነት ወሰን፣

ይህ ደንብ በአዋጅ ቁጥር 119/2006 አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 2 ጎ-አ መሰረት የኦዲት ባለሙያዎችን ወይም የሂሳብ ባለሙያዎችን በተመለከተ የሙያ ፈቃድ መስጠትን ፣ ማደስን ፣ማገድን ፣ መሰረዝን ፣ በሚመለከት ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዉስጥ በተሰማሩ ባለሙያዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ።

ክፍል ሁለት

መሰረታዊ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 5.

የተፈቀደለት ኦዲተር ተግባራት፤

1. የተዘጋጁ የሒሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት ይሰጣል ፡፡

2. የሂሳብ አያያዝ ፤የፋይናንስ እና ኦዲት ስልጠናዎችን መስጠት፤

3. የኦዲት፤የሂሳብ እና የንብረት ግብይት አስተዳደር ማንዋል ማዘጋጀት፤

4. የሒሳብ እና ኦዲት ስራዎች የሙያ ምክር መስጠት እና ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችን መ/ቤቱ ሲፈቅድ መስራት ናቸዉ፡፡

5.የተፈቀደለት ኦዲተር ሆኖ ለመስራት የሚያበቁ ዝርዝር መስፈርቶች እና የተፈቀደለት ኦዲተር ደረጃዎችን በተመለከተ ዝርዝሩ በአፈጻጸም መመርያ ላይ ይወጣሉ ፡፡

አንቀጽ 6.

የተፈቀደለት የሂሳብ አያያዝ የባለሙያ ተግባራት እና ደረጃዎች፤

1. የግብር/ታክስ/ ሂሳብ መስራት፤
2. የሂሳብ አያያዝ ስርዓት እና የዉስጥ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፤
3. የፋይናንስና የበጀት ዕቅድ ማዘጋጀት፤
4. የፋይናንስ ትንተና ስራ ማከናወን፤
5. ሂሳብ መዝጋት እና የሒሳብ ትክክለኛነትን ማረጋገጥ
6. የሂሳብ ሙያዊ ምክር መስጠት፤
7. የፋይናንስ መግለጫዎችን ማዘጋጀት፤

8. የሒሳብና ንብረት አስተዳደር ስራዎች ስልጠናና የምክር አገልግሎት መስጠት

9. በየደረጃቸዉ የተፈቀደለት ሂሳብ አያያዝ ባለሙያ ሆኖ ለመስራት የሚያበቁ ዝርዝር መስፈርቶች እና የተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ ደረጃዎችን በተመለከተ በአፈጻጸም መመርያ ላይ ይወጣሉ ፡፡

አንቀጽ 7.

በግል ወይም በማህበር የተፈቀደለት ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ ሊሰሩባቸዉ የሚችሉት ተቋማት ወይም መስሪያ ቤቶች፤

1. በግል ወይም በማህበር የተፈቀደለት ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ተቋማት ላይ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

ሀ) በመንግስታዊ የልማት ድርጅቶች፤

ለ) መንግስታዊ ባልሆኑ የልማት ድርጅቶች፤

ሐ) በግል ድርጅቶች፤

መ) በሕብረት ስራ ማህበር ፌዴሬሽን፤

ሠ) በመንግስታዊ መስሪያ ቤቶች፤

ረ) በልዩ ልዩ ደረጃ ያሉ ኮሌጆች፤

ሰ) በመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር፤

ሸ) በአነስተኛ እና ጥቃቅን የተደራጁ፤

ቀ) በህብረት ስራ ማህበር ዩኒየን፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)-(ቀ) ስር የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በግል ወይም በማህበር ተደራጅተዉ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ኦዲት ለማድረግ ከቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ጋር ውል መዋዋል እና ውክልና መዉሰድ አለበት፡፡

አንቀጽ 8.

የተፈቀደለት ኦዲተር እና ሂሳብ ባለሙያ ግዴታዎች

የተፈቀደለት ኦዲተር እና ሂሳብ ባለሙያ ፍቃድ ባገኘበት ደረጃ ላይ ብቻ ሙያዉ የሚጠይቀውን ስነ-ምግባር አክብሮ መስራት አለበት፡፡ ዝርዝሩ በአፈጻጸም መመርያ ይገለጻል

አንቀጽ 9

የተፈቀደለት ኦዲተር እና የሂሳብ አያያዝ ባለሙያ የደረጃ እድገት፣

የተፈቀደላቸዉ ኦዲተሮች እና የሂሳብ አያያዝ ባለሙያዎች እየሰሩበት ካለዉ ደረጃ ወደ ቀጣይ ደረጃ ለማደግ ይችላሉ ፡፡ / ዝርዝር ሁኔታዉ በአፈጻጸም መመርያ ይገለጻል /

አንቀጽ 10

ፈተና

1. የኦዲት እና የሂሳብ አያያዝ ሙያ ፈቃድ ለማግኘት የሙያ ፍቃድ ጥያቄ የሚያቀርብ ሁሉም ሰዉ የሚሰጠውን የሙያ ብቃት መመዘኛ መስፈርት ፈተና ማለፍ አለበት፡፡

2. መስሪያ ቤቱ በሚሰጠው የሙያ ማረጋገጫ ፈተና ላይ ጉዳዩ ቀጥታ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

አንቀጽ 11

ስልጠና

ከልዩ ልዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሂሳብ አያያዝ ትምህርት ወይም በሂሳብ አያያዝ እና ፋይናንስ ወይም በሂሳብ መረጃ ስርዓት ወይም በስራ አመራር ወይም በቢዝነስ አመራር ወይም በቢዝነስ ትምህርት ወይም በኮፕሬቲቭ ሂሳብ አያያዝ ወይም ከዚህ ጋር ተዛማጅነት ባለው ትምህርት፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎች ሆነዉ በደረጃ 4 የሙያ ፍቃድ ለሚያወጡ እና በኦዲት ስራ ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ እና ፈተና ላለፉ መስሪያ ቤቱ የኦዲት ሙያ የአጭር ጊዜ ስልጠና ይሰጣል፡፡ አፈጻጸሙ ሁኔታ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

አንቀጽ 12

ክትትል፤እድሳት፤እገዳ፤ ስረዛ ፤እና የታገደ የሙያ ፍቃድ ማደስ፣

መስሪያ ቤቱ በየዓመቱ የሙያ ፍቃድ የተቀበሉትን ባለሙያዎችን የክትትል ስራ ፣ የሙያ ፍቃድ እድሳት ስራ ፣ በህግ ከተደነገገዉ ዉጪ ሰርተዉ ሲገኙ የማገድ ፣ ፍቃዳቸዉን መሰረዝ እና የታገደ ሙያ ፍቃድን የማደስ ስራ የሚሰራ ሲሆን ዝርዝር አፈጻጸሙ በሚወጣዉ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

አንቀጽ13.

ጥፋት እና ቅጣት

ማንኛዉም በግል ወይም በማህበር የተፈቀደለት ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ፡-

1. የወንጀል ጥፋቶች በፌዴራል የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 44 ላይ የተደነገጉትን የወንጀል ጥፋቶች ፈጽሞ የተገኘ እና ሌሎች የወንጀል ህጎችን ፈጽሞ የተገኘ በዚህ አዋጅ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡
2. የወንጀል ወይም የፍትሀ ብሄር ሀላፊነት ይኖረዋል፡፡
3. በሚፈጸመዉ ጥፋት ለደረሰዉ ጉዳት በፍትሀ ብሔር መሰረት ካሳ ይከፍላል፡፡

አንቀጽ 14 .

የይግባኝ እና የቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት፣

1. የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመመርመር ከውሳኔ ሀሳብ ጭምር ለዋና ኦዲተር እንዲቀርብ የቅሬታ እና የስነምግባር ኮሚቴ የሚቋቋም ይሆናል፡፤

2. ዋና ኦዲተር በቀረበለት የውሳኔ ሀሳብ ላይ የሚሰጠዉ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

3. በግል ወይም በማህበር የተፈቀደለት ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ በተሰጠዉ ዉሳኔ ያልረካ ከሆነ በሀገሪቷ ወይም በክልሉ ህግ መሰረት የይግባኝ መብት ይኖረዋል፡፡

4. የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፤

አንቀጽ 15.

ክልከላ፣

1. ማንኛዉም ሰዉ በዚህ ደንብ ዉስጥ አሟልቶ የሙያ ፍቃድ ሳያገኝ በክልሉ ዉስጥ በግል ወይም በማህበር የኦዲት ወይም የሂሳብ ስራ መስራት ክልክል ነው፤

2. ማንኛዉም የተፈቀደለት ኦዲተር ፤ የሂሳብ ባለሙያ ፣ ባለሙያ ማህበር እና ፐብሊክ ኦዲተር የሙያ ፍቃድ ካወጣበት ዘርፍ በስተቀር መስራት ክልክል ነው።

3. ሌሎች ክልሎች ላይ ፍቃድ አወጥቶ ሲሰራ የነበረ የተፈቀደለት ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ ባለሙያ፤ማህበር እና ፐብሊክ ኦዲተር አጭር ምዝገባ ሳያደርግ ተመሳሳይ ስራ በክልሉ ውስጥ ማከናወን አይችልም።

4. ማንኛዉም በመንግስታዊ፤ መንግስታዊ ያልሆነ የልማት ድርጅቶች እና በግል ድርጅቶች የስራ መልቀቂያ ካላቀረበ የትኛውንም የሙያ ፍቃድ ማውጣት ክልክል ነዉ።

ክፍል ሶስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች፣

አንቀጽ 16.

መመሪያ የማውጣት ስልጣን፣

1.የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት ይህንን ደንብ ስራ ላይ ለማዋል መመሪያ ያወጣል

2.ይህንን ደንብ የሚቃረኑ ማንኛዉም ደንብ እና ልማዳዊ አሰራሮች ተፈጻሚነት አይኖራቸዉም፡

አንቀጽ 17

ዳግም ምዝገባ

ከዚህ ደንብ በፊት የተፈቀደለት ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ ወይም በማህበር ፍቃድ አዉጥቶ የሚሰሩ በዚህ ደንብ መሰረት በሚያርፍበት ደረጃ ላይ ተጣርቶ ፍቃድ ይሰጠዋል ።

20. ይህ ደንብ በቤ/ጉ/ክ/መንግስት ልሳነ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት --------- ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

----/----/2009 ዓ.ም

አሶሳ

ፍቃዱ ታደሰ

የቤ/ጉ/ክ/መንግስት ም/ቤት አፈ ጉባኤ

በቤ/ጉ/ክ/መንግስት በግል ወይም በማህበር የእዲት እና የሚሰበ አያያዝ ለሚሰሩ ባለሙያዎች የሙያ ፍቃድ አሰጣጥ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር-108/2009